Association of Ethiopians in Europe

info@ethiodiaspora.net

የኢትዮጵያዉያን ማህበር በአውሮፓ

www.ethiodiaspora.net

እኛ በአውሮፓ የሚንኖር ኢትዮጵያዊያን ባለፈው ሳምንት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል በሰሜን ዘን ጦር ላይ በተቃጣው አርሜናዊ ጦርነት እንዲሁም የዜጎቻችን ላይ በደረሰው የሞትና የመቁሰል አደጋ እጅጉን አዝነናል። እስካሁን ባሉን መረጃዎች ማሰረት ለዚህ አስከፊ ጦርነት በሰሜኑ እዝ ስር በሚገኘው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ የደረሰ ጥቃትና የንብረት መዝረፍ ሙከራ ሲሆን ለዚህም ቅጥ ያጣ ወንጀልና ትንከሳ ዋና ተጢያቂው ከፌደራላዊው መንግሥት አፈንግጠው የወጣውና መኖሪያውን በትግራይ ክልል ያደረገ ጥቂት የህውሃት ባለስልጣኖች ቡድን መሆኑን አረጋግጠናል።

ሕወሓት ገና ከአፈጣጠሩ የመገነጣጠልን ሰይጣናዊ ተልዕኮ አንግቦ ሲንቀሳቀስ የኖረ አጥፊ፣ ፀረ አንድነትና እኩልነት የሆነ ቡድን መሆኑ ይታወቃል። ይኸኛውም ጦርነት ሕወሐት በ 1967 ዓ/ ም ወደ ደደቢት በረሃ ሲገባ የፀነሰዉ በዘረኝነት አገርን ለማፈራረስ የተነሳበት የዓላማዉ ዉርስ አንዱ አካል ነዉ። ይህንንም ዓለማዉን ለማሳካት ሲል የአገራችንን አንዱን የኅብረተሰብ አካልና የሕዝቡን ቀዳሚ የእምነት ሥርዓቱን ማጥፋት ከግቦቹ ዋንኛዉ ሆነ። ለዚህም ይረዳዉ ዘንድ በይበልጥ አማራንና የኦርቶዶክስን እምነት አከርካሪዉን ማስበር ግቡ መሆኑን በየካቲት 11 ቀን 1968 ዓ/ ም በይፋ በራሱ ማኒፌስቶ አዉጀ። አዋጁንም ለማስፈፀም ይቻለዉ ዘንድ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችም ጋር አብሮ ለኢትዮጵያ ዉድቀት የሚሞቹዉን የፖለቲካ አጀንዳ ነድፎ የጎሳና የቋንቋ ፌዴረሽን ዘርግቶ ለእርስበርስ እልቂት ኢትዮጵያን ዳረጋት። በዚህም ሂደት ይህ ማርዘኛ ቡድን በዘረጋዉ መዋቅር አማካኝነትና የእጅ ሥረዎቹ የሆኑት ወሮበሎች የሕዝብ ዉክልና ሳይኖራቸዉ የመንደራቸዉን ሕዝብ የወከሉ ማስለዉ አገልጋይነታቸዉን ለፈጠራቸዉ ጌታ/ወያኔ በመታመን ኢሕአዴግ በሚል የዳቦ ስም የታዘዙትን ፈፀሙ። በሕወሃት የበላይነት ፍፁም አሃዳዊ አገዛዝን በፌዴራሊዝም ስም አነገሡ። ወያኔ ከሌለ ኢትዮጵያ የምትባል አገር አትኖሩም የሚል እምነት በብዙዎች ዘንድ እንዲያደርር አበክረው ሠሩ፣ በሂደትም ወያኔ ጠላት ያላቸዉን የአንድነት ኃይሎችን ሲጨፈጭፍና ሲያስጨፈጭፍ፣ ሲያፈናቅል፣ የእምነት ተቋማትን ሲያፈርስና ሲያስፈርስ፣ በውሸት ትርክት ጎሣን ከጎሣ እያፋጀ ለ 27 ዓመታት እንደ ብረት ቀጥቅጦ እንደ ሰም አቅልጦ፣ ለማዘርዘር የሚያታክቱ ሰቆቃዎችን በሕዝባችን ላይ ተለማመደ።

ስለሆነም እኛ በአውሮፓ የምንኖር ኢትዮጵያዊያን በአሁኑ ወቅት የመከላከያ ሰራዊታችን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር በመተባበር የሚወስዳቸውን ማናቸውም ዓይነት ወታደራዊ፣ ሰብዓዊና ሞራላዊ እርምጃዎች እንደግፋለን። በማንነቱ ተለይቶ እየተገደለና እየተገፋ ያለውን ኢትዮጵያዊ ለመታደግ ሃገራችን በምታደርግልን ጥሪ ሁሉ ከህዝባችን ጋር ተሰልፈን የሚከፈለውን ማስእዋትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆናችንን ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት መግለጽ እንፈልጋለን። ይህ ጦርነት እልባት እስኪያገኝም ድረስ የጠሚ አብይ አህመድና የኦሮሚያ ክልል መንግሥት በወለጋ ዞንና በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች እየተገደለና እየተፈናቀለ ላሉት የአማራና የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ወገኖቻችንን ትኩረት ሰጥተው አስቸኳይ የደህንነት ጥበቃና ዋስትና እንዲረግላቸው በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ! ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ
የኢትዮጵያዉያን ማኀበር በአዉሮፓ (ጥቅምት 27 ቀን 2013 ዓም). 09-11-2020 (GC)